የሚከተለውን አንቀፅ አንብባችሁ ከተራ ቁጥር - እስከ ላሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል ትክክለኛውን ምረጡ። እንገዶቹን የሚቀበሉበት ዋና እልፍኛቸው በሚገባ ተዘጋጅቷል። በየማዕዘኑ ሦስት መሶበ ወርቆች ቁጭ ብለዋል። ..... እስከ የገርጌ እስከ የገረጌአቸው የሚጀቡን ጃኖ ለብሰው። አጠረ ያለ የሳራ ገበታ፣ መካከል ገደማ ተዘርግቷል። ባንድ ፊት ባመቀመጫና ንቅሳታም ሸክናዎች፣ ባንድፊት ብርጭቆዎች ተደርድረውበታል።

218 አንቀፁ በዋናነት የሚገልጎው ሃሳብ የያዘው አማራጭ ከሚከተሉት የትኛው ነው?

A. የምንባቡን ገፅታ C. የባህላዊ ዕቃዎች ገጽታ

B. የእነግዶች ገጽታ D. የእልፍኝ ገጽታ

219 በአንቀፁ ውስጥ የተጠቀሰው ባሕላዊ ሥነ-ሥርዓት ከሚከተሉት አማራጮች የትኛው ነው

A. ግብዣ B. ሠርግ C. ጅጊ D. መታሰቢያ

220 አንቀጹ የቀረበበትን የአጻጻፍ ስልት የሚጠቁመው የትኛው አማራጭ ነው

A. ቀስቃሽ B. አመዛዛኝ C. ስዕላዊ D. በያኝ

221 የሚከተሉት ተዘበራርቀው የተፃፉት አረፍተ ነገሮች ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ቢፃፉ የተሟላ አንቀጽ ያስገኛሉ። ይህንን መሠረት በማድረግ ከተራ ቁጥር - እስከ ላሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጡ።

1. በዚህ የድምፅ ብክለት ሳቢያም እንደጆሮ መደንቆር፣ የመስማት ኃይል መቀነስ እና የሰላም መታወክ ጠንቆች ከዋነኛ ችግሮች መካከል የሚጠቀሱ ሆነዋል።
2. ለምሣሌ፡- የውሃ የአየረ የአፈረና የድምፅ ብክለት መኖር ከተሞችን ለሰው ልጅ ኑሮ ተስማሚ እንዳይሆኑ እያደረጋቸው ነው።
3. ከከተሞች ዕድገት ጋር በቁርኝት አብሮ እየገዘፈ ከመጣው ችግር አንደኛውና ዋናው የበክለተ ተግር ነው።
4. በተለይ ከላይ ከተጠቀሱት ብክለቶች መካከል የድምፅ ብክለት በአዱስ አበባ አንደ አንድ ችግር የሚተይ ሆኗል።
5. ከዚህ የብክለት ችግር የተነሳ ከተሞች ለሰው ልጅ ኑሮ ተስማሚነታቸው አሣሣቢ እየሆነ መጥቷል።

South West Academy

222 ከላይ ከተጠቀሱት አረፍተ ነገሮች መካከል በአንቀጹ መጀመሪያ መምጣት የሚገባው ዋና አረፍተ ነገር ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?

A. አንደኛው አረፈተ ነገር
C. አራተኛው አረፍተ ነገር
B. ሦስተኛው አረፍተ ነገር
D. አምስተኛው አረፍተ ነገር

223 ከላይ ከተጠቀሱት አረፍተ ነገሮች መካከለ በአንቀጹ መጨረሻ መምጣት ያለበት አረፈተ ነገር ከሚከተሉት አማራጮች መካከለ የትኛው ነው?

A. አንደኛው አረፈተ ነገር
C. አራተኛው አረፈተ ነገር
B. ሦሰተኛው አረፍተ ነገር
D. አምስተኛው አረፍተ ነገር

224 ከላይ ከተጠቀሱት አረፍተ ነገሮች መካከለ በአንቀጹ መጨረሻ መምጣት ያለበት አረፈተ ነገር ጋር የሚያያይዘው ቃል ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?

A. ከዚህ አንፃር
B. በተለይ
C. ለምሣሌ
D. ከዚህ

225 ከላይ ከተጠቀሱት አረፈተ ነገሮች የሚመሠርቱት አንቀጽ ውስጥ ባላቸው ቅደም ተከተል መሠረት የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ጉድለት የሚታይበት ስንተኛው አረፈተ ነገር ነው?

A. አንደኛው አረፍተ ነገር
C. አሪተኛው አረፈተ ነገር
B. ሦሰተኛው አረፈተ ነገር
D. አምስተኛው አረፈተ ነገር

226 አንቀጹ በዋናነት አጉልቶ የሚያሳየው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛውን ነው?

A. ማህበራዊ ችግር
C. ተፈጠሮአዊ ችግር
B. ኢኮኖሚያዊ ችግር
D. የአሰተዳደር ችግር

227 ከላይ የተፃፉት አረፍተ ነገሮች በቅደም ተከተላቸው መሠረት የሚገኑቱት አንቀጽ የተፃፈው በየትኛው የድርስት አጻጻፈ ስልት ነው?

A. በተሪኪ
B. በቅስቀሳ
C. በአመዛዛኝ
D. በገላጭ

228 የሚከተለውን ግጥም ትክክለኛ ቅደም ተከተል የሚያሳየው አማራጭ ምረጡ።

ሀ. ጡበቀው ካልያዙት የዘነጉ ለታ
ለ. ማስሪያው ምላስ ነው የተቋጠረበት
ሐ. ይፈሳለ ምስጢሩ ማሰሪያው ሲፈታ
መ. ልብ ስልቻ ነው ምሰጢር የሞሉበት

A. ሐ፣ሀ፣ለ፣መ
B. መ፣ለ፣ሐ፣ሀ
C. መ፣ለ፣ሀ፣ሐ
D. ለ፣መ፣ሐ፣ሀ

229 ከሚከተሉት ምሣሌያዊ አነጋገሮች መካከል ስለልጅ በጎ ተርጉም ያለውን አማራጭ የያዘው የትኛው ነው?

A. ልጅና ጥሬ አይተጣጡም
C. ለጅ ያቦካው ለራት አይበቃም
B. ልጅና ጦጣ ውሃ ይጠጣ
D. ልጅን በጡት አህልን በጥቅምት

230 «ጆሮ ስጠኝ ቢለው ጆሮም የለኝ አለው።» ለዚህ አባባል ትክክለኛ ትርጉም ሊሆን የሚችለው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?

A. ላዳምጥህ ቢለው አልነግርህም አለው።
B. አዳምጠኝ ቢለው አልስማህም አለው።
C. መስሚያ ስጠኝ ቢለው መስሚያህ ይበጠስ አለው።
D. ሹክ በለኝ ቢለው ጀሮውን ነፈገው

ግጥሙን በትኩረት ካነበባችሁ በኋላ ለእየነዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማሪጮች መካከል ተገቢውን መልስ ምረጡ።

ፈልቀሽ የተገኘሽ ከሹበርት ራስ፣
ከቤቶቬን ናላ ከመዛር መንፈስ፣
ከፐን ትካዜ ከያሬድ ልቦና፣
መዓዛ የሞላብሽ የብስጭት ቃና፣
ረቂቋ ድምፅ ሆይ ውቢቷ ሙዚቃ፣
ንፁህ አንደ ፀሐይ ውብ እንደጨረቃ።

South West Academy

ከበደ ሚካኤለ። 1999 የዕውቀት ብልጭታ። አ.አ ሜጋ አሣተሚ፣ ገፅ 125

231 ከላይ ለተፃፈው ግጥም ርዕስ ሊሆን የሚችለው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?

A. ሙዚቃ B. ጨረቃ C. ፀሐይ D. ውቢቷ

232 የአምስተኛው ስንኝ መነሻ ሐረግ የሆነው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?

A. መዓዛ የሞላበሽ C. ውቢቷ ሙዚቃ

B. ረቂቋ ሙዚቃ D. ረቂቋ ድምፅ ሆይ

233 በግጥሙ የመጀመሪያ ስንኝ ላይ የሚገኘው «ፈለቀሽ» የሚለው ቃል የግጥሙን ዜማ ወይም ምጣኔ እንዲጠበቅ መነበብ ያለበት እንዴት ነው?

A. ጠበቆ B. ላልቶ C. ቀልሞ D. ረቆ

234 ሙዚቃ ከጨረቃ ጋር የተነፃፀረችው በምንጠቁመው ከሚከተሉት አማራጮች የትኛው ነው?

A. በንፅሕና B. በቃና C. በውበት D. በመዓዛ

235 ግጥሙ ሰንት መነሻ እና ሰንት መድረሻ ሐረጎች አሉት?

A. ስድስት መነሻ እና ስድስት መድረሻ ሐረጎች አሉት።

B. ስድስት መነሻ እና አስር መድረሻ ሐረጎች አሉት።

C. ስድስት ሰንሾችና አስራ ሁለት ሐረጎች አሉት

D. ሰባት መነሻ ሐረጎችና ስምንት መድረሻ ሐረጎች አሉት።

236 የተሚላ ሐሣብ ማስተላለፍ የሚችሉት በየትኛው ቅደም ተከተል የተሚሉ ከሆነ ነው?

ሀ “ይቅርታ” ሀ “ስንት ሰዓት እንደሆነ ልትነግሪኝ ትችያለሽ?”

ለ"_____" ለ"_____"

ለ “አዎ” ለ” ምንም አይደል!”

A. ሰዓት ይዘሻል? አቤት? ይቻላል፣ አመስግናለሁ!

B. አቤት? ይቸላል፣ ሰዓት ይዘሻል አመሰግናለሁ!

C. አቤት? ሰዓት ይዘሻል ይቻላል፣ አመስግናለሁ

D. አመስግናለሁ፣ ሰዓት ይዘሻል? አቤት፣ ይቻላል

237 ከዚህ በታች በተፃፈው አንቀጽ ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች በቅደም ተከተል በትክክል ሊያሟሉ የሚችሉትን ሐሣቦች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጡ።

የተለያዩ ጽሑፎችን በማንበብ የንባብ ጥሜን አረካለሁ። አንድን ጽሑፍ አንብቤ ግንዛቤ ለመጨበጥ ከፊለግሁ በ_____የንባብ ስልት አጠቀማለሁ።ጽሑፉን በጥልቀት ማንበብ ካለብኝ ደግሞ በ _____አነባለሁ። በሌላ በኩል የአንዳንድ ጽሑፍ አጠቃላይ ሐሣብ ለማግኘት የማነብ ከሆነ የ_____የአነባበብ ስልትን እመርጣለሁ።

A. አሰሳ፣ ገረፋ ገረፋ፣ ዝግታ

B. ዝግታ፣ ገረፋ ገረፋ፣ አሰሳ

C. ገረፋ ገረፋ፣ አሰሳ፣ ዝግታ

D. አሰሳ፣ ዝግታ፣ ገረፍ ገረፍ

238 የሚከተለውን ምልልስ ካነበባችሁ በኋላ ለተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት የሆነው ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጡ።

“ሃሎ !ሃሎ! ሐረገወይን ነሽ?”

“አዋን ማን ልበል?”

“ትናንት ሰምቼ በጣም ነው ያዘንኩት .....”

“ይቅርታ ማን ልበል?”

“አሁንም እዚያው ቢሮ ነሽ አይደለም”

239. ሐረገወይን ስልኩን ጆሮው ላይ ዘጋችበት።

A. ሐረገወይን የደወደወለላትን ሰው በድምፁ አለመለየቷ

B. ሐረገወይን ችግሯን የሚያስወግድላት ሰው አለመፈለጓ

C. ሐረገወይን የደወለላትን ሰው ማንነት አለማወቋ

South West Academy

D. ሐረገወይን ትዕግሥት ያልፈጠረባት ሴት መሆኗ

240. “ምኝ ገበሬ አውሬ ሲያድን በሬውን አውሬ ያስበላል።” የሚለው አገላለጽ ከሚከተሉት መካከል ከየትኛው ጋር በትርጉም ይመሳሰላል?

A. አተርፍ ባይ አጉዳይ

B. አለባብሰው ቢያረሱ በአረም ይመለሱ

C. ተንጋለው ቢተፉ ተመልሶ ባፉ

D. በቅሎ ግዙ ግዙ አንድ ጨው ላያገዙ

241. “ምን ቢያርሱ እንደ ጐመን_____።”ይህንን ጅምር ምሣሌያዊ አነጋገር ሊያሟላው የሚችለው የትኛው ነው?

A. አይቀንጥሱ B.አይነሰንሱ C. አይጎርሱ D. አይነሰንሱ

242. ከታች የተፃፈው አንቀጽ የቀረበበት የአፃፃፍ ስልት ምን እንደሆነ የሚያመለክተው አማራጭ የትኛው ነው?

ፀጥታና ዝምታ በመዝገብ ቃላት ፍቺያቸው ተተካኪ ቢሆኑም መጠነኛ ልዩነት አላቸው። ፀጥታ ሰላም የሰፈነበት የአእምሮ እረፍትን ያመለክታል። ሁከትን ሳይሆን ውስጣዊ እርጋታን ስለሚጠቁም ስሜትን ያዝናናል። ዝምታ ግን እፎይታን ሊያሳይ ይችላል። በዝምታ ውስጥ የገዛ ራስ ጉርምርምታ ሊኖር ይችላል።

A. ንፅፅር B. ትንተና C. ትረካ D. ምዘና

243. ማደመጥን አስመልክቶ አዎንታዊ ሐሣብ ካላቸው መካከል የተለየው የትኛው ነው?

A. ጨዋታን አዳምጦ እህልን አላምጦ

B. ጆሮ የሰማውን ልብ ያውቀዋል

C. ያልሰማ ጆሮ ከጎረቤት ያጣላል

D. የነገር ወጡ ማዳመጡ

244. የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ተዘበራርቀው ተፅፈዋል። ከታች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ ቅደም ተከተላቸውን የያዘው የትኛው ነው?

ሀ. አረጋሽም ሻንጣዋን ይዛ ታክሲ ውስጥ ገባች

ለ. ትንሽ እንደተራመች “መገናኛ! መገናኛ!” እያለ አንድ ታክሲ አጠገቧ ቆመ።

ሐ. ዳሜ ጠዋት አረጋሽ ልብሶቿ በሻንጣ ከታ የህና ዋሉ ብላ ወጣች።

መ. ትንሽ እንደሄደች ታክሲውን እንዲቆምላት ጠይቃ ወረደች።

A. ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ መ C. ሐ፣ ለ፣ ሀ፣ መ

B. ሐ፣ ለ፣ መ፣ ሀ D. መ፣ ለ፣ ሀ፣ ሐ

245. አንድ ዛፍ አለ፤ አሥራ ሁለት ቅርንጫፎች አሉት፤ እያንዳንዱ ቅርንጫፍ ስላሣ ቅጠሎች አሉት።” ለሚለው እንቆቅልሽ መልስ የሚሆነው ከሚከተሉት አማራጮች A. A. መካከል የትኛው ነው?

A. ሰው፣ የዘር ሐረግ፣ ትውልድ

B. ዓመት፣ ወራት፣ ቀናት

C. ሀገር፣ ብሔረሰቦች፣ ሰዎች

D. መንግሥት፣ ክፍለ ጦር፣ ወታደር

246.“አይንና አፈር” ብሎ “ፀበኞች” ካለ “ለመጠቃቃት የሚጠባበቁ ጠላቶች” ብሎ _____ይላል።ክፍት ቦታውን ሊያሟላ የሚችለውን ሐሳብ ለሚከተሉት መካከል የትኛው ነው?

A. አህያና ጅብ C. አይጥና ድመት

B. ውሻና ድመት D. አህያና ፈረስ

247. ቤት ሲሠራ ዋናውና ብርቱ ጥንቃቄ የሚያስያስፈልገው መሠረቱ ነው።

መሠረቱ ያልጠነከረ ቤት እድሜ አይኖረውም። ቤት የሚሠራ ሰው ሁሉ ለመሠረቱ ጥንካሬ ቅድሚያ መስጠት ይኖርበታል።

ከላይ የተፃፈው አንቀፅ ከሚከተሉት መካከል ለየትኛው የድርሰት ዓይነት ምሳሌ ሊሆን ይችላል?

A. ተራኪ B. አመዛዛኝ C. ገላጭ D. ቀስቃሽ

South West Academy

248.ሰኞ በአሥራ ሁለት ሰዓት ተገናኝተው ወደ ስድስት ኪሎ ጉዞ ጀመሩ።
የዕለቱ አየር ቀዝቀዝ ያለ ስለነበር ብዙም ድካም አልተሰማቸውም። በስሱ የሚነፍሰው ነፋስ ውብቆት የዋለውን ሁሉ እያረካ የመንገዱን ዳር ትርኢት ረጋ አድርጎታል።
ከላይ የተፃፈው አንቀፅ ከሚከተሉት መካከል ለየትኛው የድርሰት ዓይነት ምሳሌ ሊሆን ይችላል?
A. አመዛዛኝ B. ተራኪ C. ስዕላዊ D. አስረጅ
249.ያልተሟላ ምሣሌያዊ አነጋገር በቅደም ተከተል በትክክል ማሟላት የሚችለው የትኛው ነው?
A. የቀበረ፣ የነበረ C. የወረረ፣ የፈጠረ
B. የነበረ፣ የቀበረ D. የወገረ፣፣የበረረ
250. “የተተከለው አበባ ውሃ ባለመጠጣቱና ባለመኮትኮቱ የሚፈለገውን ያህል አላደገም” በሚለው ሐሳብ ውስጥ የመንስኤ ሐሳቦቹ ምንድን ነው?
A. ውሃ አለማጠጣትና አለመኮትኮት
B. ውሃ አለማጠጣትና አለመኮትኮት
C. አለመኮትኮትና አለማደግ
D. የአበባው ተተክሎ አለማደግ
ግጥሙን በትኩረት ካነበባችሁ በኋላ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ተገቢውን መልስ ምረጡ።
ባለማሰብ ገመድ ተይዞ ተጠልፎ፣
ደንዝዞ ከመኖር ኑሮን አስተዳደፎ፣
እንደዕውር ከመሄድ ውብ አይናማ ሆኖ፣
ምነው ቢታይበት ሁሉንም አፋጥኖ።
መሥራት ነውር ሲሆን ጥበብም ተንቃ
251. ቀኑ ይጨልማል_ _____።
ግጥሙ ውስጥ ያሉት መነሻና መድረሻ ሐረጎች ስንት ናቸው?
A. 15 B. 6 C. 13 D. 12
252. ለጣሚው ለተደስያን ለማስተላለፍ ከፈለገው መልዕክቶች መካከል ልዩ የሆነው የትኛው ነው?
A. ገንዘብን አናፍቅር፣ በሥራ እንመን
B. አባይን እንገድብ፣ ድህነት ይልቀቀን
C. ሥራን እናክብር፣ ኑሯችን ይሻሻል
D. በሥራ እንጠመድ፣ ስንፍና ይወገድ
253.የግጥሙ ሦስተኛው ስንኝ መነሻ ሐረግ ከሚከተሉት መካከል የትኛው ነው?
A. እንደ እውር ከመሄድ ውብ
B. በመሄድ ውብ አይናማ ሆኖ
C. እንደ እውር ከመሄድ
D. እንደ እውር ከመሄድ ውብ አይናማ
254.የግጥሙ እንደ ችግር ከሚያነሳቸው መካከል ልዩ የሆነው የትኛው ነው?
A. ማስተዋል ሲቻል መደንዘዝ
B. ማየት ሲቻል አለማየት
C. መራመድ ሲቻል መደንዘዝ
D. አለመጠቡብ ሲቻል መንቃት

255.ያልጠረጠረ ተመነጠረ» በሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር መንስኤ የሆነው ድርጊት የትኛው ነው?
A. አለጠርጠር C. መጠርጠር
B. መመንጠር D. ጥርጣሬ

South West Academy

256. «እዩኝ እዩኝ ማለት ደብቁኝ ማለትን ያስከትላል» በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ለድርጊቱ ውጤት የሆነው የቱ ነው
A. እዩኝ ደብቁኝ C. አትዩኝ አትደብቁኝ
B. እዩኝ እዩኝ D. ደብቁኝ ደብቁኝ
257. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ቅደም ተከተሉን የጠበቀ የድርጊት መመሪያ የትኛው ነው?
A. የንባብ ፍላጎት ማሳደር፣ መጽሀፍ መምረጥ፣ በታመምረጥ፣ ተደላድሎ ማንበብ
B. መጽሀፍ መምረጥ፣ የንባብ ፍላጎት ማሳደር፣ በታ መምረጥ፣ ተደላድሎ ማንበብ
C. በታ መምረጥ፣ የንባብ ፍላጎት ማሳደር፣ መጽሀፍ መምረጥ፣ ተደላድሎ ማንበብ
D. መጽሀፍ መምረጥ፣ በታ መምረጥ፣ የንባብ ፍላጎት ማሳደር፣ ተደላድሎ ማንበብ
258. ከሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች መካከል ብልህነትን የሚያወድስ የትኛው ነው?
A. ሁለት ጉድጓድ ያላት አይጥ አትሞትም
B. ቀን በበቅሎ ማታ በቆሎ
C. ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ
D. ዝናብ ሲያባራ ወደ ዋሻ
259. ከሚከተሉት መካከል የባሰ ነገር ማጋጠሙን የሚያመለክተው ምሳሌያዊ አነጋገር የትኛው ነው?
A. የእነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ
B. ሥራ ያጣ ሙቅ ያላምጣል
C. ቀና ሲታጣ ይመለመላል ጎባጣ
D. ከእሳት ወደ ረመጥ
260. ከዚህ በታች የተጻፉት አረፍተ ነገሮች ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ቢጻፉ አንድ አንቀጽ ይወጣቸዋል።ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን ቅደም ተከተል የሚያሳው የትኛው ነው?
1. ይህ ጥናት አንድ ሰው አንድ ተግባር ሲያከናውን የእጅ እንቅስቃሴ እያንዳንዱን ክንውን ለመጨረስ ስንት ሴኮንዶች እንደሚወስድ ያሳያል።
2. እነዚህ ባልና ሚስት ተመራማሪዎች የሚታወቁት በጊዜና እንቅስቃሴ ጥናት ነው።
3. ብርዜና አቶ ምሳ ባልና ሚስት የነበሩ ተመራማሪዎች ናቸው
4. ባልና ሚስቶች ህይወታቸውን በሙሉ ያሳለፉት የዚህ ዓይነት ቀልጣፋ የአሰራር መንገድ ለመፈለግ ነው።
A. ልጅ ካባቱ ሾተል ካፎቱ
B. ልጅና ጦጣ ውሃ ይጠጣ
C. ልጅና ወረቀት የያዘውን አይለቀም
D. ልጅና እህል እያደር ይበስላል
261. “ባለችው መጠቀም ጥሩ ነው” የሚለውን በምሳሌያዊ አነጋገር ለመገለጽ ከሚከተሉት የትኛው ተስማሚ ነው?
A. ከበላ ብላ ከሰው አትጣላ። B. ምጡን እርሺ ልጅን አንሺው
C. ማምሻም አድሜ ነው። D. ሞኝ አሞራ ያባቱን ዋሻ ይጠየፋል።

262. ከሚከተሉት ስነ-ቃሎች መካከል እንቆቅልሽ የሆነው የትኛው ነው?
A. ሲከተሉት የሚርቅ ሲርቁት የሚከተሉ
B. ሽክላ ቢጥሉት ገለባ
C. የሚሰርቀውን ያጣ ሌባ ሰላማዊ መስሎ ገባ
D. ሆዱን ያለ ሆዱን ተወጋ
263. “ማር ቀምሼ አላውቅም እኔ ወንድማችሁ፣ ያገሬ ወጣቶች ተማሩ እባካችሁ።” በሚለው ግጥመ ውስጥ ሁለት የተለያዩ ትርጉሞች የያዘው የትኛው ነው?
A. ወጣቶች B. ወንድማችሁC. አላውቅም D. ተማሩ
264. “ሳቅ በሁለት ሰዎች መካከል ያለውን ወሰን ይሰብራል። አላስፈላጊ ጭንቀቶችን ያረግባል። ፈገግታን ይፈጥራል። ችግሮችን ይቋቋማል።” የዚህ ጽሁፉ ዋና ሃሳብ የተገለፀው በየትኛው አማራጭ ነው?
A.የጭንቀት መርገብ C. የፈገግታ መፈጠር

South West Academy

B. የሳቅ ጠቀሜታ D. የችግር መወገድ

265. በአንድ በተለመደ ሰዓት ምንም ይሁን ምን መመገብ እንደሚያስፈልግ የሚገልፀው አባባል ከሚከተሉት መካከል የትኛው ነው?

A.ሆድና ግንባር አይሸሽግም C. ሆድ ያበላውን ያመሰግናል

B. ሆድ እንዳሳዩት ነው D. ሆድ ባዶ ይጠላል

263. ተዘበራርቀው የተቀመጡትን የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች በቅደም ተከተለ የያዘው አማራጭ የትኛው ነው?

1. መካሻ ዛሬ በህይወት የለም።
2. መካሻ በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደ።
3. በመቀጠል አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ በመማር የአረትስ ባችለር ዲግሪውን አግኝቶ እዚያው በመምህርነት ለብዙ አመታት አገለገለ።
4. ከዚያም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የአንድ አመታት የመምህርነት ግዳጁን ተወጣ።
5. ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስ ትምህርት ቤት ገብቶ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ከመምህራን ስልጠና ጋር አጠናቀቀ።

B. 5፣3፣2፣1፣4 B. 2፣3፣5፣4፣1

C. 2፣5፣4፣3፣1 D. 2፣4፣2፣3፣5፣1

264. ከላይ በተራ ቁጥር -- በቅደም ተከተል እንዲቀመጥ የተደረገው ሀሳብ ምን ላይ ያተኩራል?

A. ልብወለድ C. የህይወት ታሪክ

B. ቃለጉባዔ D. ድርሰት

265. የሚከተሉት ተዘበራርቀው የተቀመጡት አረፍተ ነገሮች በየትኛው ቅደም ተከተለ ቢቀመጡ የተቀናጀ እንቀጽ ይፈጥራሉ?

1. ከዚህ ቀጥሎ ጥሩ ድንጋዮች እንዳይነቃነቁ ተደርገው ተርታውን በተቆፈረው ቦታ ውስጥ ይቆማሉ።
2. የቤት መሰረት የሚያርፍበት ቦታ በሃምሳ ሴንቲ ሜትር ስፋት ይቆፈራል።
3. ከዚያም የተረበረበው ድንጋይ እንዲጠናከር አሸዋና ሲሚንቶ ተቀላቅሎ ከተቦካ በኃላ ይደረግበታል።
4. በመቀጠል ኮረትና አነስተኛ ድናጋዮች በቆሙት ድንጋዮች መካከል የሚታዩትን ቀዳዳዎች እንዲደፈኑ ይደረጋል።

A. 2፣1፣4፣3 C. 2፣4፣1፣3

B. 2፣3፣1፣4 D. 2፣3፣4፣1

266. ከዚህ በታች የተጻፈው አንቀጽ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ለየትኛው ምሳሌ ይሆናል?

ኢትዮጵያን ከመስከረም እስከ ነሐሴ ያሉት አሰራ ሁለት ወራት በምክንያታዊ ትርጉም

ሲሰይሙ አውሮፓውያን ግን ያመልኳቸው የነበሩትን ጣኦታት መሰረት ያደረጋል። ለምሳሌ ሰኔ የተሰኘው ወር ስኂየ ከሚል ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም አማረ ማለት ነው። የአውሮፓውያን ስድስተኛው ጁን ግን ስያሜ ያገኘው ጁኖ ከምትባለው የሰርግ ወይም የጋብቻ አምላክ ነው።

A. ተራኪ ድርሰት C. ገላጭ ድርሰት

B. አመዛዛኝ ድርሰት D. የቅስቀሳ ድርሰት

ዓለሙን ጠፍጥፈው ቂጣ በጋገርሁት
ውሃውን ጨምቄ ቅቤ _____።
ባወጣሁት ቅቤ ቂጣዬን አርሼ
ጨጨብሳ ጭብጦ አድርጌ ለውሴ
አንዴ በገመጥሁት አንጀቴን ባራስሁት።
ምኞት ፈረስ ሆኖ የሽምጥ አይሄድም
ደንገላሳ አይመታም ሶምሶማም አይረግጥም
በህገ ተፈጥሮ በታሪክ ስራቱ
ዓለም እንደወትሮው ዓለም እንደጥንቱ።

South West Academy

የኢትዮጵያ ደረሲያን ማህበር። 1999 የዘመን ቀለማት የግጥም መድበል። ቅፅን ከገፅ 19 ተመጥኖ የተወሰደ።

267.ከላይ የቀረበው ግጥም ከሚከተሉት ሀሳቦች የትኛውን ያጠናክራል?

A. ምኞት ያለ ተግባር ዋጋ ቢስ ነው።

B. ምኞት ከተፈለገው ግብ ያደርሳል።

C. ምኞት የህይወት መሻሻልን ያስገኛል።

D. ምኞት እንጀት ያርሳል

268.. ግጥሙ በስንት ስንኞችና ሀረጎች የተገነባ ነው?

A. በ 8 ስንኞችና በ 16 ሀረጎች C. በ 10 ስንኞችና በ 18 ሀረጎች

B. በ 9 ስንኞት በ 18 ሀረጎች D. በ 9 ስንኞችና በ 17 ሀረጎች

የግጥሙ ደራሲ በግጥሙ ውስጥ ምኞትን ለመግለጽ በዋናነት የተጠቀመበት ቃል ምንድን ነው?

A. ቅቤ B. ዓለም C. ተፈጥሮ D. ፈረሰ

269. ገጣሚው ማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት መካከል የትኛው ነው?

A. ምኞት የተፈጥሮ ህግጋትንና የህይወት ገጽታን መለወጥ ይችላል።

B. ምኞት ያሰቡትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያገለግል መሳሪያ ነው።

C. ምኞት የተፈጥሮ ህግጋትም ሆነ ዓለምን የመለወጥ አቅም የለውም

D. ምኞት ቅቤ ያሰበላል፤ አንጀት ያርሳል፤ ሆድ ይሞላል

270. . በሁለተኛው ስንኝ በተተወው ባዶ ቦታ ላይ ቢገባ የግጥሙን ሀሳብና ምጣኔ የተሟላ የሚያደርገው ከሚከተሉት የትኛው ነው?

A. ባወጣሁት B. በተቀባሁት C. ጠጣሁት D. በነካሁት

271.ያለአቅም መንጠራራትን ለመግለፅ ተስማሚ ሊሆን የሚችለው ምሳሌያዊ አነጋገር ከሚከተሉት መካከል የትኛው ነው?

A. ዕንቁራሪት ዝሆንን አክል ብላ ተሰንጥቃ ሞተች።

B. አህያ ሲጠግብ ከጅብ ይጫወታል።

C. የማታድግ ውርንጫላ እናትዎን ትመራለች።

D. የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል።

272.. ‹‹ሁለት እግር አለኝ ተብሎ _____።›› ይህንን ጅምር ምሳሌያዊ አነጋገር ከሚከተሉት በየትኛው መቋጨት ይቻላል?

A. ሁለት መኪና አይነዳም። C. ከአቅም በላይ አይሮጥም።

B. ሁለት ዛፍ አይወጣም። D. ሁለት ኳስ አይመታም።

273. ‹‹ሆይ! ይላል ገበሬ፣
ሆይ! ይላል ገበሬ
ድብ እያፈረሰ በሻልማ በሬ››

የሚለው የዘፈን ግጥም ከሚከተሉት በየትኛው ውስጥ ይመደባል?

A. ከስራ ዘፈን C. ከክብረ በዓል ዘፈን

B. B. ከሰርግ ዘፈን D. ከልጆች ጨዋታ ዘፈን

274. ‹‹ፈረ ጨነቀው ተርበደበደ
ጥይት ዘነበ እሳት ወረደ
ውረድ እንውረድ ተባባሉና
አስደበደቡት አፋፍ ቆሙና›› የሚለው

275. ከሚከተሉት የስነ-ቃል ዘርፎች መካከል ለየትኛው ተስማሚ ነው?

A. ሙሾ B. ልመና C.እንጉርጉሮ D. ፉከራ

ጥያቄ ቁጥር **112** እና **113** በሚቀጥለው አንድ አንቀፅ ጽሁፍ ላይ የተመሰረቱ ናቸው ጽሁፉን በትኩረት አንብባችሁ ለጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጡ።

South West Academy

‹‹ያን ክፉ ቀን አትረሳውም። የዛሬ ስምንት ወር ገደማ ከገበያ ስትመለስ ልጇን አጣችው። ከአካባቢ ልጆች ጋር ሊጫወት ሄዷል ተባለች። ዓይኗ ደጅ ደጁን እያየ መጨለም ጀመረ። ኋላም ልጆቹ ተደናግጠው እየተንጫጩ መጡ። ልጇን አውሬ እንደበላው አረዷት። ከማንም ቀድማ ነጠላዋን ጥላ በረረች።

276.. ከላይ የተፃፈው አንቀጽ ውስጥ ዋናው ሀሳብ የተገለፀበት ዓረፍተ ነገር የትኛው ነው?

A. ከማንም ቀድማ ነጠላዋን ጥላ በረረች C.ልጇን አውሬ እንደበላው አረዷት

B. ከገበያ ስትመለስ ልጇን አጣችው D. ያን ክፉ ቀን አትረሳውም።

277. አንቀጽ ከሚከተሉት አማራጮች መካከል በየትኛው ስልት የተፃፈ ነው?

A. በትረካ B. በገለፃ C. በአመዛዛኝ D. በስዕላዊ

278. የሚከተሉትን ተዘበራርቀው የተፃፉት አረፍተ ነገሮች ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ቢፃፉ የዳስ አሰራር ሂደትን ያመለክታሉ ከታች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ሂደቱን በትክክል የሚያሳየውን
ምረጡ።

ሀ. ከዚያም ዳርዳሩን አለፍ አለፍ ተብሎ ጉድጓዶቹ ይማሳሉ። በጉድጓዶቹ ላይም ጠንከር ያሉ ባለባላ ወጋግራዎች ይተከላሉ።

ለ. በመጨረሻም ጣራው ፀሀይ እንዲከላከል ሰንበሌጥ ወይም ጨፈቃ ይለብሳል።

ሐ. በመጀመሪያ ለዳሱ መስሪያ በተመረጠው ቦታ ላይ ቁጥቋጦ ካለ ተመንጥሮ ይፀዳል።

መ. በመቀጠልም በወጋግራዎቹ ግራና ቀኝ እንዲሁም አናት ላይ ቀጠን ቀጠን ያሉ ጠርቦች ከማገር ጋር በልጥ ይዋደዳሉ።

A. ሐ፣ሀ፣መ፣ለ B. ሐ፣መ፣ለ፣ሀ C. ሐ፣መ፣ሀ፣ለ D. ሐ፣ሀ፣ለ፣መ

279. የሚከተሉት ተዘበራርቀው የተፃፉት አረፍተ ነገሮች በቅደም ተከተል ቢቀመጡ የስራ ሂደት ቅደም ተከተልን ያሳያሉ። ከታች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን ሂደት የያዘውን ምረጡ።

ሀ. ዘሩ በንፋስ እንዳይጠረግ በቅጠል ሸፍኖ በማጠጣት ተንከባከበው።

ለ. ችግኙ ከመሬት ብቅ ብሎ እንደታየ ቅጠሉን አነሳ።

ሐ. መሬቱን በመቆፈር መደብ አዘጋጀ።

መ. ችግኙ እያደገ መጥቶ ለተክል ደረሰ።

ሠ. በመደቡ ላይ የባሕርዛፍ ዘር ዘራ።

A. ሠ፣ሀ፣ለ፣ሐ፣መ B. ሀ፣ሠ፣ሐ፣ለ፣መ C. ሐ፣ሠ፣ሀ፣ለ፣መ D. ሐ፣ሀ፣ሠ፣ለ፣መ

280.‹‹የፈሰሰ ውሃ አይታፈስ ፤ ወደሌላ ጎንበስ።›› የሚለውን ሀሳብ በምሳሌያዊ አነጋገር አጉልቶ ለመግለፅ ከሚከተሉት የትኛው ተመራጭ ነው?

A. ምጡን እርሽው፤ ልጁን አንሺው።

B. ክሰር ያለው፤ ቢነግድ አያተርፍ።

C. ከሰው ስህተት፣ ከብረት ዝገት አይጠፋም።

D. ቅጥፖት ተፈርቶ፣ ሳይተኛ አይታደርም።

281. ቀጥሎ የተፃፈውን አንቀጽ በትኩረት በማንበብ የተፃፈበትን ስልት ከተሠጡት አማራጮች መካከል ምረጡ።

ገበሬ አለበት ቦታ ላይ በእግሩ ተደላድሎ የሚቆም ነው። ምንም እንኳን የቆመበት መሬት የርሱ ባትሆንም ከላይዋ ላይ መቆሙ ይሰማዋል፤ የመሬት ምንነት ለስሜቱ ይታወቀዋል። የፋብሪካ ሰራተኛው ግን እንደወፍ ነው። እኔ የበቀልኩበት ነው የሚለው የራሱ መሬት የለውም። ዛሬ እዚህ ቢገኝ፣ ነገ ይህንን የነበረበትን የስራ ቦታ ለቅቆ ይሄዳል፤ የተሻለ ፍለጋ ከቦታ ቦታ ይናውዛል። ገበሬ ግን ከወዲያ ወዲህ ሳይባክን የኑሮ ሁኔታው የተሻሻለ እንዲሆንለት እዚያው ባለበት ረግቶ ይቀጥላል።

A. የትረካ ስልት B. የገለፃ ስልት C. የማወዳደር ስልት D. የትንተና ስልት

ከጥያቄ **118** እስከ **122** ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ግጥም ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ግጥሙን በትኩረት ካነበባችሁ በኋላ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ተገቢውን መልስ ምረጡ።

እንደ ዳመና ጓል ታይቶ እንደሚበተን

South West Academy

የአንድ አፍታ ክስተት ነው ህይወት ሲተነተን።
በዓለም ብዙ ሆኗል አልፏል ተከውኖ
አሻራ እየተወ ‹‹ነው›› ‹‹ነበር›› ን ሆኖ።
በጊዜ ስንክሳር ታሪክ ሆኖ ፋና
መልካም ስራ አይሞትም ሚችን ይሸኝና።
ጊዜ ሳይሽራቸው ሳይገታቸው ድንበር
ታሪክ ሲሆኑ ክብር ሀቅና ቁም ነገር።
ይቺን ጥቂት ነገር መስራት እያቃተው
ከንቱ ይቀራል ሰው መታሰቢያ ሳይተው።

ምንጭ፡- የኢትዩጵያ ደራስያን ማህበር (1999)። የዘመን ቀለማት።
ገጽ 53 በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ።

282. ከላይ የተፃፈውን ግጥም ከሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች በየትኛው ማጠቃለል ይቻላል?
A. ለስሚ መጥሪያ ቁና ሰፋች። C. ጊዜ ሲያመልጥ ሲመለጥ አይታወቅም።
B. ስም ከመቃብር በላይ ይውላል። D. ላይቀር ሞቴ ክፉ መስራቴ።
283. በግጥሙ ውስጥ ስንት ስንኝ ግጥሞች አሉ?
A. 5 B. 6 C. 8 D. 10
284. የግጥሙ አራተኛ ስንኝ መነሻ ሀረግ ከሚከተሉት የትኛው ነው?
A. አሻራ እየተወ ‹‹ነው›› C. አሻራ እየተወ
B. ‹‹ነው›› ‹‹ነበር›› ን ሆኖ D. ‹‹ነበር›› ን ሆኖ
285. በአራተኛው ስንኝ ውስጥ የተጠቀሱት ‹‹ነው›› እና ‹‹ነበር›› ምንን ያመለክታሉ?
A. ሕይወትን B. አሻራን C. ዓለምን D. ጊዜን
286. በቀረበው ግጥም ውስጥ ስለሚታየው ምጣኔ ምን ማለት ይቻልል?
A. የግጥሙ ሀረጋትና ስንኞች እኩል የሆነ ምጣኔ አላቸው።
B. የግጥሙ ሀረጋትና ስንኞች ምጣኔ እኩል አይደለም።
C. የግጥሙ ምጣኔና ምት የተስተካከለ ባለመሆኑ ዜማ የለውም።
D. ግጥሙ በሀረጋትና በስንኞች ምጣኔ አይለካም።

<u>አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ</u>
<u>የአንደኛ ደረጃ ትምርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ፈተና ሰኔ **2002** ዓ.ም</u>

ክፍል አንድ

መመሪያ አንድ፡- ከጥያቄ 1 እስከ 10 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

287. የምንባቡ የመጀመሪያ አንቀጽ ከሚከተሉት አማራጮች መካከል በየትኛው ይገለፃል?
A. አንቀጹ ታሪኩ የተፈፀመበትን ቦታና ጊዜ ይገልፃል።
B. አንቀጹ የደቡብ ሕዝቦችን ባህላዊ ሁኔታን ይገልጻል።
C. አንቀጹ ባለታሪኮችን የድርጉት አንቀስቃሴ ይናገራል።
D. አንቀጹ ባለታሪኮችን የድርጊት እንቅስቃሴ ይናግራል።
288. በመንባቡ ሁለተኛ አንቀጽ ውስጥ “ጥላ” እና “ሃና”
A. ተመሳስለዋል B. ተነፃፅረዋል C. ተፎካክረዋል D. ተፈቃቅረዋል
289. በጽሑፉ የቀረበው ምንባብ የተጻፈበት የድርሰት አይነት ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?
A. የቅስቀሳ ድርሰት B. አመዛዛኝ ድርሰት C. ተራኪ ድርሰት D.አስረጅ ድርሰት
290. “የአካሏ ጥበቀት ወዟና ጠይምነቷ <u>ወከከ ያደርጋል።</u> በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሠመረበት ሐረግ ትርጉም ምን እንደሆነ የሚያመለክተው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?
A. ልብ ይሰረስራል B. ልብ ይሰነጥቃል። C. ልብ ይለበልባል። D.አስረጅ ድርሰት
291. ጋሻው ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ጉዞ ያደረገው ለምን እንደሆነ የሚገልፀውን ሃሳብ የያዘው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?
A. ከሃና ጋር ለመዝናናት C. የበና ቆንጆዎችን ለማየት
B. ተፈጥሮን ለማድነት D. ፎቶግራፍ ለማንሳት

South West Academy

292. የበናዋ ቆንጆ በጋሻውና በሃና እንቅስቃሴ ምን እንደተሰማት የሚገልፀው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?

A. ንድት B. ደስታ C. ህመም D. ፍርሃት

293. ከሚከተሉት አንዱ የበናዋ ቆንጆ ከተጠቀመችበት ጌጣጌጥ መካከል አይገኝም። የትኛው ነው?

A. ቀለበት B. ሌቲ C. አልቦ D. አምባር

294. በምንባቡ ሐሣን መሰረት የሐመር፣ የበናና የማሊ ጎሣዎችን የሚያመሳስላቸው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው

A. ልብስ የማይጠቀሙ መሆኑ C. ማህበራዊ ባህላዊ አካባቢ የሌላቸው መሆኑ

B. ባህላዊ ዕቃ የሌላቸው መሆኑ D. የሚታወቁበት ቋንቋ የሌላቸው መሆኑ

295. ጋሻው በፎቶግራፍ ማንሳት የሰለጠነ ስለመሆኑ በዋቢነት የቀረበው ከሚከተሉት አማራጮች የትኛው ነው?

A. ከፍታ ላይ ሆኖ ፎቶ ማንሳቱ C. በ 12 ኪ/ሜ ላይ ፎቶ ማንሳቱ

B. በካሜራ ሌንስ ሳይጠቀም ፎቶ ማንሳቱ D.በጫካ ውስጥ እየተሽለኮለከ ፎቶ ማንሳቱ

296. የበናዋ ጉበል ፀጉርዋን የምታስውበው በምን እንደሆነ የሚገልጎነው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?

A. ቫዝሊን B. ቅቤ C. ቀይ አፈር D. ሞራ

እሁድ፣ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት፣ 2000 ዓ.ም።በደቡብ የኢትዮጵያ ክልል ከጂንካ ሃያ ኪሎ ሜትር ወጣ ብሎ ቃቆ የምትባል ቦታ ላይ።

“ከምድር እኩል የተፈጠረው ንፁህ አየር ይሽውልሽ” አለ ጋሻው እንደጥላ የምትከተለው ሃናን እያየ።

“እንዴት ደስ ይላል! የተራራው አቀማመጥ፣ የዛፎቹ አቋቋም፣ የወንዞቹ አወራረድ” አለች ዙሪያ ገባውን እየተመለከተች።

“በዚህ ቃቆ የምትባል አካባቢ በና የሚባል የጎሳ መጠሪያ ያላቸው ኢትዮጵያውን ይኖራሉ። ወዲያ ማዶ ደግሞ ማሊ የሚባሉ አሉ። ታዲያ የሁለቱም ጎሳ አባላት ልብስ የሚባል ነገር አያውቁም። እንዲያው ሀፍረታቸውን ለመሸፈን ያህል ትንሽዬ ቆዳ ያንጠለጥላሉ።”

“ከቡስካ በስተጀርባ የተባለው መጽሐፍ ውስጥ እንዳሉት ሐመሮች?”

“አዎ አንብበሽዋል?”

“ እንዴ? ለዛውም ደጋግሚነዋ”

“ ብራቮኒ”

ረጅሙን የዙም ሌንስ በዘመናዊ ካሜራው ላይ እየገጠመ “አሁን እስከ ሁለት ኪሎ ሜትር ርቀት ድረስ ማንሳት እችላለሁ” አላት። በጣም ተደነቀች። ወንዙ ዳር ያለችው ዛፍ ላይ ወጣና ወዲያ ማዶ ላይ አነጣጠረ ምንም የለም። ወዲያ አነጣጠረ እንደዚያው። ዱብ ብሎ ወረደ።

በዛፉና ቅጠላ ቅጠል መሃል እየተሽለኮለኩ በሳቅ እየተፍነከነኩ እንድ ገላጣ ቦታ ብቅ አሉ።እፍረቷ አካባቢ ብቻ ሦስት ማዕዘን ቁርበት ጣል ካደረገች የበና ልጃገረድ ጋር ተፈጠጡ። ደንግጣ እንደሐውልት ድርቅ አለች። የበናዋ ቆንጆ ጡቶቿ ለመተኮስ የተወደሩ ሮኬቶች ይመስላሉ። በቀይ አፈር የታሰው ፀጉርወ ቁልቁል ይጥመዘመዛል። ከቀላል ብረት የተሰሩ ሦስት ቀለበቶች በአንገቷ ዙሪያ ተጥምጥመዋል። ሃና አፏን ከፈተች። የበናዋ ቆንጆ ተክለሰውነት ትንግርት ሆኖባታል። የአካሏ ጥብቀት ወሂና ጠይምነቷ ወከክ ያደርጋል።

ጋሻው ቀስ ብሎ ጣቶቹን ከካሜራው ጋር አገናኘ። ልጃገረዲቱ ሃናን በአይኖቿ ወጋቻት። ጀሮዎቷም ትልልቅ ሎቲዎችን አንጠልጥለዋል። ክንዶቿም ካላይ እስከ ታች በመዳበና ቀላጭ ብረቶች አጊጠዋል።

የጋሻው፣ የሃና፣የበናዋ ጉበል የልብ ትርታ ቆሟል። የዓይን ርግብግት ሳይቀር ተቋርጧል። የበናዋ ቆንጆ ፊት ላይ ሳያደረግ በግምት በማንሳት ተክኗል። የበናዋ ጉበል አፈገፈገች። የሃና ዓይኖች ልጃገረዲቱ ባዶ እግሮች ላይ አረፉ። አልቦዎቿ አንፀባረቁባት። ጉበሊቱ አፈገፈገች። ጋሻው የካሜራውን መምቻ ተጫነ። ቀጭ!ቱር አለች እንደሚዳቋ።

ጋሻው ዘሎ ከፍታ ላይወጣ። ካሜራው ዓይኑ ላይ ነው። በሌንሱ ውስጥ የጉበሊቱ ምስል ይርመሰመሰል። “ከሞን” ይላል ጋሻው ሌንሱን ዞር ቀጭ!ዞር ቀጭ! በተከታታይ የካሜራውን መምቻ ተጫነው ፊልሙ ሲያልቅ ቆመ። በፍጥነት ቀይሮ አነጣጠረ የበናዋ ቆንጆ የለችም። በመጪው ዓመት ካናደ፣ ቱሮንቶ ውስጥ የሚካሄደው

South West Academy

ዓለም አቀፍ የፎቶ ግራፍ ውድድር አሸናፊነቱን ደመነፍሱ ከወዲሁ ሹክ አለችው። ምንጭ ልዑል ግርማ 2000 “ለማሸነፍ” የኢትዮጵያደራሲያን ማህበር የሥነ-ጽሑፍ መጽሔት። ብሌን ፰፡ገፅ 16።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማጠቀቂያ የአማርኛ ፈተና ሰኔ **2004** ዓ.ም

ክፍል አንድ

መመሪያ አንድ፡- ከጥያቄ 1 እስከ 10 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሠረት ትክክለኛው መልስ ምረጡ።

297. የሁለተኛው አንቀፅ የመጀመሪያ አረፍተ ነገር “ብራ በሆነበት አንድ ሐሙስ……” ብሎ ይጀምራል። “ብራ” ማለት ምን ማለት ነው?
   A. አህያ የማይችለው ዝናብ የመጣበት ቀን
   B. ውሽንፍር የቀላቀለበት ዝናባማ ቀን
   C. ዝናብ ሳይጥል የቀረበት ቀን
   D. አቧራማና ነፋሻማ ቀን

298. በሦስተኛው አንቀፅ ውስጥ ያይኔአበባ “የዋሽንት ልጅ ናት” የሚል ተጠቅሷል። ይህ ማለትምን A. ማለት እንደሆነ የሚጠቅሰው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?
   B. ዋሽንት ለያይኔአበባ እንደወላጅ አባትና እናት የሚቆጠር የሕይወት እስትንፋስ መሣሪያ ነው ማለት ነው።
   C. ዋሽንት ለያይኔአበባ ከፅንሰት እስከ ልደት፣ ከልጅነት እስከ ዕውቀት ከነፍስና ከደሟ ጋር ተዋህዶ ያለ ማለት ነው።
   D. ዋሽንት በአያይኔአበባ ሕይወት ውስጥ በመጨረሻ ዘመንዋ መተዳደሪያዋና ፈጣሪዋ የሆነ ማለት ነው።

299. የምንባቡ የመጀመሪያ አንቀጽ ከሚከተሉት አማራጮች በየትኛው የአፃፃፍ ስልት የተስፋፋ ነው
   A. በገለፃ ስልት B. በትረካ ስልት C. በማነፃፀር ስልት D. በትንተና ስልት

300. ማህበረሰቡ የተዋጣላቸውን ባለሙያዎች የሚገባቸውን ክብርና ሞገስ እንዳያገኙ የማጥላላት ዘመቻ እንደሚያካሂድ የተገለፀበት አንቀጽ ስንተኛው ነው?
   A. ሁለተኛው B. ሦስተኛው C. አራተኛው D. አምስተኛው

301. በምንባቡ ውስጥ ከህብረተሰቡ አጉል እምነት በተቃራኒ ቆሞ የሚታየው ባለታሪክ ማን እንደሆን የሚገልፀው አማራጭ የትኛው ነው?
   A. ያይኔአበባ አባት B. ማየት የተሣነው C. ያይኔአበባ D. አንዷለም

302. በምንባቡ ሦስተኛው አንቀጽ ውስጥ “ቁንዝላ” የሚል ቃል ቃል ተጠቅሷል። ቁንዝላ ምንድነው?
   A. የዋሽንት ስም B. የዛገ አውሊያ ስም C. የመንደር ስም D. የልክፍት ስም

303. ለምንባቡ ርዕስ ሊሆን የሚችለው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?
   A. የዋሽንት ፍቅር B. ያይኔአበባ C. የሙዚቃ ሙያ D. ባህልና ሕብረተሰብ

304. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ያይኔአበባ የብሩ ደምበኛ የሆነችበትን ምክንያት የሚገልፀው የትኛው ነው?
   A. በብሩ ውስጥ አባቷን መመልከቷ
   B. ብሩ ሰው ወዳጅና አክባሪ መሆን
   C. በብሩ ችሎታ የስሜቷ መቀስቀስ
   D. የብሩ ደምበኞች ብዛት

305. የሚከተሉት ተዘበራርቀው የተፃፉት አረፍተ ነገሮች በቅደም ተከተል ሲፃፉ ያይኔአበባን የሕይወት ታሪክ ያመለክታሉ። ትክክለኛውን ያይኔአበባን የሕወት ታሪክ በቅደም ተከተል ያያዘው የትኛው አማራጭ ነው?
   1. የሙዚቃ ባለሙያ ሆነች።
   2. በዋሽንት መጫወት ችሎታዋ ተቃውሞ ገጠማት።
   3. ያይኔአበባ ገና በእናቷ ማህፀን እያለች ዋሽንትን ከደሟ ጋር አዋሃደች።
   4. እሃቷ ዋሽንት መጫወቷን ልታስቆማት በተለያየ መንገድ ሞከረች።
   5. ዋሽንት መጫወትን ከአባቷ እየተማረች አደገች።
   A. 1፣2፣3፣5፣4 B. 3፣5፣2፣4፣1 C. 2፣4፣3፣5፣1 D. 2፣5፣3፣4፣1

306. በሕብረተሰቡ አጉል እምነት ምክንያት መገለል የደረሰበት ወይም የደረሰባት ማን እንደሆነ ወይም እንደሆነች የሚያመለክተው አማራጭ የትኛው ነው?
   A. ያይኔአበባ አባት
   B. የወባ መከላከየው አንደለም
   C. ማየት የተሳነው ባለዋሽንት
   D. ያይኔአበባ እናት

South West Academy

ምንባብ

የዘንድሮ ዝናብ መላቅጡ ጠፍቶ ያይኔአበባንም መላቅጥ አሣጥቷታል። አንዳንዴ ማምሻው ላይ ሰማዩ በፉጠሪካ ጥቀርሻ የጠቆረ ይመስል ያኮርፍና ዶፋ ያለቅሳል። ሲያሰኘው ደግመ ደመና መጋረጃውን ፈገግ ይላል። በጢያሣ የመንገድ ኩረንቲ ብርሃን ወጋገንም ይፈካል።

ብራ በሆነበት አንድ ሐሙስ የትይንት ጥበባት ፕሮግራም እንዳለቀ የሙዚቀኛ ልብሷንና ፍሉቷን ለግምጃ ቤት እንዲያስረክቡላት አደራ ሰጥታ እየተደፈች ፈትለክ። ታክሲው ከጢያሣ መናኸሪያው እንዳደረሳት ዓይኗን ወደ ማዘጋጃ ቤት ሜዳ አካባቢ ወረወረች። ከመንገድ ዳር እጅብጅብ ብለው የሚቆሙትን በርካታ ሰዎች እንዳየች ልቧ የደስታ ደወል አቃጨለች። የዋሽንቱን ድምፅ ከሩቅ እንደሰማች የውስጥ አካሏ በፍንደቃ ንጥረ ነገር ተሞላ። የዋሽንት ልጅ ናትና።

ያይኔአበባ ከመፀነሷ በፊት በእናቷና ባባቷ ደም ውስጥ የዋሽንት ዜማ በየምሽቱ ተንቆርቁሯል። ኋላም በእናቷ ጆሮ በኩል ዘልቆ ከሽልነቷ ተዋህዷል። የማህፀኑ ምጆት አጓጉቶዋት አልወጣም ብላ ከእናቷ ጋር ስትታገል፣ አባቷ ከሁለቱም ጭንቀት ለመራቅ እቤቱ ጓሮ ከጣና ወደብ ላይ ሆኖ ዋሽንቱን ፑሉሉ! ሲያደርግ ነበር በመጀመሪያ ለቅሶ ከቁንዝላ መንደር የተዋወቀችው። ወተትን ከዋሽንት ዜማ ጋር ተመግባም ነው ያደገችው። እናት ወተትን ከጡት ከጡትዋ በአፍ፣ አባት ዜማን ከሽንበቆው በጆሮ ባንድነት በመልቀት። ሥራ የጀመረችውም እንድር በስታ ዋሽንት በመሥራት፣ ጥናት የቀፀለችው አቧቷ ጉልበት ላይ ተቀምጣ ዋሽንት ከከንፈሯ አስጠግቶ "ኡፍበይበት" ሲላት "ኡፍ" በማለት ነው። ጥቡበን የተካነችው ቅድስት እስትንፋሷን በዋንት ቀዳዳ በኩል እየኰረኰረች በማሳቅ፣ በደስታ ሲቃ ፈንድቃ ከአባቷ አንገት ላይ በመጠምጠም ግንባሩን፣ ጉንጩን፣ በመሳም ፍቅርን ከመልካም ውጤት በማጐዳኘት በዋሽንት ነው ሰውነቷን መቅረፅ የጀመረችው።

" የዛጐፍ አውሊያ ሰፍሮባታል..... ቡዳ ናት ..... ስታድግ ዘማ መሆኗ ነው...." ነበር መደምደሚያቸው ይህ ነበር ለጋ አእምሮዋን የሚያመሳቅለው። እናትየወ በሷ ሳቢያ ከሐብረተሰቡ

በመራራቋ ዋሽንት ልታሰቆማት በሳማ፣ በለበቅ፣ በአኰርማጅ ለብልባታለች። ጠበል አስጠምቃታለች። ክታብ አሥራላታለች።ከልክፍቱ ሊያላቅቃት የቻለ ግን አልነበረም። የዞኑ የወባ መከላከያ ኃላፊ እንደለም ብቻ ነበር አበጀሽ የሚላት። ከባሕር ዳር ሲመላለስ በጂፕ መኪናው ከከተማው ወጣ እያደረጋት "በይ ተጫወች። ዋሽንት የመላዕክት ቋንቋ ነው።" የሚላት። ከዚያም አዲስ አበባ ወስዶ ያሬድ አስገብቶ በፍሉት መሣሪያ በከፍተኛ ነጥብ ያስመረቃት። ባለሙያነት ያበቃት።

አንደ ቀን ምሽት ልብ የሚሰውር የዋሽንት ዜማ ከሩቅ ተጉዞ፣ በመስኮት ጉበቶ ሰማች። ድምፁን ወደሰማችበት ሄዳ ክብብ ብለው የቆሙትንና የተቀመጡትን እየገፋፋች ወደፊት ቀረበች። ከጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ዋሽንቱን የሚደቡበሰውን ማየት የተሣነውን ወጣቱን መለከቀና አይታ ድንግጥ አለች። አምና ያረፉትን አባቷን በውስጡ ተመለከተች። የብሩ ደምበኛም ሆነች።

አቦነህ አሻግሬ 2000 ዕንቁጤ-እንቁጣጣሽ
እና ሌሎች ልቦለዶች። አዲስ አበባ።

<u>አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ፈተና</u>

<u>ሰኔ 2005</u>

<u>ክፍል አንድ</u>

መመሪያ አንድ ከጥያቄ 1 እስከ 11 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

307. ከላይ ለተፃፈው ምንባብ ርዕስ ሊሆን የሚችለው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛ ነው? □

A. የአዲስ አበባ ገፅታ
B. አዲስ አበባና ገፅታ
C. አዲስ አበባና የጣሊያን ወረራ
D. የአዲስ አበባ ስያሜ

308. የአዲስ አበባ ከተማ አመሠራረት ሂደት የተጀመረው መቼ እንደሆነ የሚገልፀው ሐሳብ የሚገኘው በምንባቡ ስንተኛው አንቀፅ ላይ ነው?

A. በአንደኛው
B. በሁለተኛው
C. በአራተኛው
D. በአምስተኛው

309. በምንባቡ ሐሣብ መሠረት አንደ ኢትዮጵያ አቆር በ 1928 ም ስለተፈጠረው ክስተት A. A. የሚገልፀው አማራጭ ከሚከተሉት መካከል የትኛው ነው? □ □ □

B.ኢትዮጵያ አድዋ ላይ ጣሊያንን ድል አድርጋለች።
C. አንዳንድ የአዲስ አበባ መሠፈሮች የጣሊያንኛ ስያሜ አግኝተዋል
D. ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግስታት ጋር ዲፕሎማያሲያዊ ግንኙነት መስርታለች

South West Academy

309. በምንባቡ የተፃፈበትን ዘመን ዋቢ አድርጎ በመጥቀስ በአሁኑ ጊዜ አዲስ አበባ ከተቆረቆረች ምን ያህል ዓመት ሆኗታል ብሎ መናገር ይቻላል?

A. መቶ ዓመት C. ሁለት መቶ አምስት ዓመት

B. አንድ መቶ አምስት ዓመት D. አያሌ መቶ አመታት

310. እንደምንባቡ ሐሳብ መሠረት በአዲስ አበባ ለሚገኙ ሠፈሮች ስያሜዎች መነሻ ተደርጎ የተወሰደውን ሐሳብ የያዘው አማራጭ ከሚከተሉት የትኛው ነው?

A. የጠላ ወረራ፣ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትና የሕዝቦች አስፋፊር

B. የጉልተኞች አስተዳደር ፣ የነፃነት ጥያቄና ማህበራዊ ኑሮ

C. የተለያዩ አጋጣሚዎች፣ ክስተቶችና ታሪካዊ ክንዋኔዎች

D. የነፃነት ፍቅር፣ አልበገር ባይነትና የኔነት ስሜት

311. በምንባቡ ውስጥ በሰፈረው ሐሳብ መሠረት ትክክለኛ ጥንድ ሊሆን የሚችለው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?

A. ሙሴ ሰርኪስና ካዛንቺስ C. ፈረንሳይ ሌጋሲዮንና የጦር ምርኮኞች

B. የጣሊያን ወረራና ጣሊያን ሰፈር D. ተረት ሰፈርና ሙሴ ቴረስ

312. ምንባቡ የተፃፈበት ዓላማ ምን እንደሆነ የሚገልው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?

A. አዲስ አበባ የተቆረቆረችበትን ዘመን መግለፅ

B. አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ ሰፈሮች ስያሜ አመጣጥን መግለጽ

C. አዲስ አበባ የአህጉራዊና ዓለማቀፋዊ ድርጅቶች ከተማ መሆኗን መዘከር

D. አዲስ አበባ የብሔር ብሔረሰቦች መናኸሪያ ከተማ መሆኗን መዘከር

313. የምንባቡ ሁለተኛ አንቀፅ ጋር የተያያዘው ከሚከተሉት በየትኛው አያያዥ ቃል ነው?

A. በሌላ በኩል B. በሌላ ዘርፍ C. በሌላው መንገድ D. በሌላ መስመር

314. ከቀረበው ምንባብ ለወጡት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ከሚከተሉት የንባብ አይነተች መካከል የትኛውን መጠቀም ግድ ይላል?

A. የአሰሳ ንባብ C. የገረፍ ገረፍ ንባብ

B. የፍጥነት ንባብ D. የዝግ ንባብ

315. በምንባቡ ሐሳብ መሠረት ለአዲስ አበባ ሰፈሮች ስያሜ መገኘት የቀረቡት ሐሳቦች ምን ያህል

316. እንደሆኑ የሚገልፀው አማራጭ ከሚከተሉ የትኛው ነው?

A. ስድስት B. ሰባት C. ስምንት D. ዘጠኝ

317. ምንባቡ ከዚህ ከቀረቡት አማራጮች መካከል የየትኛው ጽሑፍ ምሣሌሊሆን ይችላል?

A. የፈጠራ ጽሑፍ C. የማስታወቂያ ጽሑፍ

B. የኢልብ ወለድ ጽሑፍ D. የአፈ ታሪክ ጽሑ

<u>ምንባብ</u>

ከተመሠረተች አያሌ ዓመታት ያስቆጠረችው አዲስ አበባ በርካታ ታሪካዊና ዘመናዋ ሠፈሮች አሏት። የአዲስ አበባ ሠፈሮች ምሰረታ ሂደት የተጀመረው አራት ኪሎ በሚገኘው የዳግማዉ አሄ ምኒሊክ ቤተመንግስት ወይም በዘመኑ አጠራር ግቢ ከተገነባ በኋላ ነው። ይኸውም ሂደት የተጀመረው እንደኢትዮጵያ አቆጣጠር 1900 ዓ.ም ወይም የዛሬ 100 ዓመት ገደማ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ ሠፈሮች ከላይ ከተጠቀሰው ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ ስያሜያቸውን ያገኙት በተለያዩ ምክንያቶችና አጋጣሚዎች ነው። በርካታዎቹ የከተማዋ ቀደምት ሠረሮች ስያሜያቸውን ያገኙት በቤተ መንግስቱ ዙሪያ መሬት በጉልት መልክ በተሰጣቸው መሣፍንትና መኳንንት ስሞች ነበር። ጥቂት የማይባሉ የአዲስ አበባ ሠፈሮች ደግሞ ስያሜያቸውን ያገኙት በተለያዩ አጋጣሚዎች ክስተቶችና ታሪካዊ ክንዋኔዎች ነው። ለምሣሌ ሠባራ ባቡር ሠፈር ከነዚህ መካካል ይጠቀሳል። ይህ ሠፈር ስያሜውን ያገኘው ሙሴ ሰርሲስ ተርዚያን በሚባሉ አርመሃዊ ነጋዴ አማካኝነት ከውጭ አገር መጠቶ አሁን ስያሜውን ባገኘበት ቦታ ተበላሽቶ በቀረው የመንገድ መስሪያ ተሽከርካሪ ምክንያት ነው።

South West Academy

በሌላ በኩል ከአድዋ ጦርነት በኋላ በድለ አድራጊው የኢትዮጵያ ሠራዊት የጦር ምርኮኞች የሆኑት የጣሊያን ተወላጆች በማረፊያነት የተመረጠው ቦታ ጣሊያን ሠፈር የሚለውን ስያሜ ማግኘቱ ይታወቃል። ሌላው በከተማው ከሚገኙ ዋና ዋና ሠፈሮች መካከል በከተማዋ ቀደምት ነዋሪዎች በሆኑት የኦሮሞ ተወላጆችና የቦታ ስሞች የተሰየሙ ሠፈሮችን እናገኛለን። ከነዚህመ መካከል ጉለሌና የካ ሰፈሮች ተጠቃሽች ናቸው።

በሌላ ዘርፍ ከ 1928 ዓ.ም የጣሊያን ወረራና የአምስት ዓመት ቆይታ ጊዜ አንዳንድ የአዲስ አበባ ቦታዎችና ሠፈሮች የጣሊንኛ ስያሜ አግኝተዋል። ከነዚህም መካከል መርካቶ፣ ፒያሳ፣ ካዛንቺስን መጥቀስ ይቻላል። እንዲሁም በከተማዋ በሚገኙ አብያተ ክርስትያንና አጥቢያዎች መካከል ተቀዳሚውን ሰፍራ የሚይዘው አራዳ ጊዮርጊስ ነው።

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ከ 1888 ዓ.ም የአድዋ ጦርነት ድል በኋላ ጣሊያንና ሌሎች የአውሮፓ መንግስታትና አሜሪካ የአገራችንን ሉዓላዊነት በመቀበል ዲፕሎማስያዊ ግንኙነት ከመሠረቱ በኋላ አንዳንዶቹ ሠፈሮች ስያሜያቸውን ከኤምባሲዎቹ አግኝተዋል። ለዚህም ፈረንሣይ ሌጋሲዮንና ሩዋንዳ ሠፈሮች ምሣሌዎች ናቸው። ከአዲስ አበባ ከተማ ሠፈሮች መካከል አንዳንዶቹ በታዋቂ የውጭ አገር ዜጎች ስም የተሠየሙ ይገኛሉ። ከነዚህመ መካከል ቤኒን እና ተረት ሠፈሮች ይገኙበታል። ቤኒን ሠፈር ስያሜውን ያገኘው ከጣሊያን ወረራ በፊት ታዋቂ ነጋዴ በነበሩት ቤኑን ከተባሉት የአይሁድ ተወላጅ ሲሆን ተረት ሰፈር ደግሞ በአዲስ አበባ ከተከፈቱት የመጀመሪያ ሆቴል ቤቶች አንዱ ከነበረው የሆቴል ዳፍራንስ ባለቤት በሆኑት ፈረንሳዊ ሙሴ ቴረስ ስያሜውን አግኝቷል።

<u>የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ፈተና **2006**</u>

<u>ክፍል አንድ</u>

መመሪያ አንድ፡- ከጥያቄ 1 እስከ 11 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላየ የተመሠረቱ ናቸው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

318. የምንባቡ የመጀመሪያ አንቀጽ የሚጎድለው የሥርአተ ነጥብ አይነት የቱ ነው
A. ድርብ ሰረዝ C. አራት ነጥብ
B. ነጠላ ሰረዝ D. ትእምርተ አንክሮ

319. “ጥቢ” ለሚለው ቃል የሚስማማው ፍቺ የትኛው ነው?
A. በጋ ውጭ ግንቦት C. ክረምት ውጭ መስከረም
B. በልግ ውጭ ሰኔ D. ፀደይ ውጭ ሕዳር

320.የምንባቡ የመጀመሪያ አንቀጽ ስለምን ይናገራል?
A. ስለ ክረምቱ ማለፍ C. ስለክረምት መግባት
B. ስለክረምት አስቸጋሪ መሆን D. ስለክረምት እየከበደ መምጣት

321. በሁለተኛው አንቀፅ ውስጥ በተገለፀው መሠረት የፀሐይ መኩራራት መንስኤ ምንድነው?
A. የክረምት መወለድ C. የክረምት ማየል
B. የፀሐይ መንገስ D. የደመና አለመኖር

322. በምንባቡ ውስጥ በትልቅ ሉል የተመሰለቸው ምንድናት?
A. ጨረቃ B. ፀሐይ C. አዲስ አበባ D. መሬት

323. ምንባቡ የትኛውን የድርሰት አፃፃፍ ስልት የተከተለ ነው?
A. ተራኪ B. አመዛዛኝ C. ገላጭ D. አስረጅ

324. በምንባቡ የመጀመሪያ አንቀጽ “ቆይ ደሞ እንገናኛለን” የሚለው ሐሣብ የቀረበው በምን ዓውድ ነው?
A. በመተሳሰብ B. በዛቻ C. በሰላምታ D. በመሰነባበት

325. “ኧረ ጥራኝ ዱሩ” በሚሉት አይነት ብሶት ያለበትን ሰው እንደሚያባብል የተነገረለኝ ነው?
A. የአደይ አበባ የከበሮ ድልቂያ C. ችምችም ብሎ የበቀለው ደን
B. የድሮው አይሮፕላን ማረፊያ D. የመናገሻ ተራራ ረጲን ጨምሮ

326.በምንባቡ ሐሣብ መሠረት የጀንበር ማሽቆልቆል ምንን ያመለክታል?
A. ቀኑ መዳመኑን C. ቀኑ ተሰያት መሆኑን
B. ቀኑ መጨለሙን D. ቀኑ መምሸቱን

South West Academy

327. አራተኛው አንቀፅ በዋናነት የሚያጎላው ሐሣብ ምንድነው
A. በአዲስ አበባ የአግረኛና የመኪና ብዛት
B. የአዲስ አበባ የእግረኛና የመኪና ብዛትን
C. የአዲስ አበባ የመንገድ ዳር መብራቶች መድመቃቸውን
D. የአዲስ አበባ የመንገድ ዳር መብራቶች መድመቃቸውን

328. በቀረበው ምንባብ ውስጥ ሚልኪያስ ፍኖትን የምንተዋወቀው በምን ቦትና ጊዜ ነው?
A. በሳሎን ውስጥ በአመሻሽ
B. በአትክልት ስፍራ በፀሐይ መጥለቂያ
C. በቤት ውስጥ በጥቢ ፀሐይ
D. በአዲስ አበባ በመስከረም

ምንባብ

ክረምት የልቡን ሠረቶ "እንዲህ ነኝ እኔ ወንዱ!" እየተጎማለለ እየፎከረ "ቆይ ደግሞ እንገናኛለን" እያለ እየዛተ እያሰፈራራ ሥፍራውን ለጥቢ ፀሐይ እየለቀቀ ጓዙን ጠቅልሎ መሄድ ጀምሯል።

ተነፋፍቀው የሰነበቱት መሬትና ፀሐይ ቆሎ የሚጣጣቡም አይመስሉ። ጨራሯን ሙሉ በሙሉ መሬት አንዳታዳርስ ከልከለኦለት ከመሬት ጋር አኮራርፏት የከረመው ደመና ሲገፍ ፀሐይ በበቸኝነት የምትኩራራ ትመስላለች። አዲስ አበባን የከበቡት ተራሮች በአደይ አበባ አሸበርቀው ጀንበር ስታዘቀዝቅ በሚሸኟት ደማቅ ቀለማት ተውበው ከተማቸውን ዙሪያውን ከበው የሚደለቁ ይመስላሉ። መስከረም ሲያልቅም "መስከረም ጠባዬ" እያሉ ይዘፍናሉ። ወፎች አልልታውን ያስነኩታል።

ከድሮው አይሮፕላን ማረፊያ ባሻገር በጀርባው የረጲንና የመናገሻን ተራራ ተገን አድርጎ ችምችመ ብሎ የበቀለው ደን እሱመ የአደይ አበባውን የከበሮ ድልቂያና ጭብጨባ የሚከተል የራሱን እስክስታ ጀምሯል። ወደ አንድ ወገን ጋደል ይልና ቀና እንደገና ወደሌላ ወገን ጋደም..... አንድ ላይ። በተለይ አንጋጠው ሲመለከቱት በተለይ ብሶት ያለበትን ሰው ያባብላል" ኧረ ጥራኝ ዱሩ" በሚሉት አይነት።

የአዲስ አበባ ግርግር መሸትም ሲል አያባራ፣ አንዳውም ይበስበታል። አግረኛውመ መኪናውመ ይርመሰመሳል። የመንገድ ዳር መብራቶች አዲስ አበባን ማድመቅ ጀመረዋል። ልጆች "የሰማይ አምፑል" እያሉ የሚጠሯት ጨረቃ ግዙፍ ሉለ መስላ ከአዲስ አበባ በስተምሥራቅ አድማሱ ጥግ ልጥፍ ብላ ትታያለች።

ሚልኪያስ ፍኖት የሳሎኑን ስስ መጋረጃ ገለጠና ወደውጭ ተመለከተ። ከግንቡ አጥር ውጭ ሊታየው አልቻለም። አረንጓዴ ቀለም የተቀባው የአጥር የብረት በር እንደተዘጋ ነው። የግቢው ልዩ አበቦች የጀንበሯን ማሽቆልቆል የሚቃወም ሰልፈኛ መስለው ተርታውን ተሰልፈው ግራ ቀኝ ይወዛወዛሉ። ሚልኪያስ አይኑ ሊደርስበት የቻለውን ሁሉ እሰኪበቃው ቃኘና ሰዓቱን ተመለከተ። አሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል።

ምንጭ፡- ሰለሞን ለማ፡- 1982። ጐሚ። አዲስ አበባ፣
ኩራዝ አሣታሚ ድርጅት ከገጽ 169 – 170 በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ፈተና **2007**

ክፍል አንድ

መመሪያ አንድ ከጥያቄ **1** እስከ **12** ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ለእያንዳንድ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

329. በአሸንዳ በዓል በዋናነት የሚሳተፉት እነማን ናቸው?
A. ወንዶች
B. እናቶች
C. ልጃገረዶች
D. ትዳር የፈቱ ሴቶች

330. የአሸንዳ በዓል የመስክ በዓል ነው ሲባል ምን ማለት ነው?
A. በቤት ውስጥ ይከበራል ማለት ነው።
B. ከቤት ውጭ ይከበረል ማለት ነው።
C. በክረምት ይከበራል ማለት ነው።
D. ነህሴ ውስጥ ይከበራል ማለት ነው።

331. በአሸንደ በዓል የቡድን መሪወ ተግባር ምንድን ነው
A. ዘፈን ማውጣት
B. ከበሮ መምታት
C. ዘፈን መቀበል
D. ስጦታ መያዝ

332. ሴራ-ሚዜ የሚባሉት እነማን ናቸው?
A. የአንድ ሀገር ልጆች
B. አብሮ አደግ ልጃገረዶች
C. የአሸንዳ ሴቶች
D. ከበሮ

333. የአሸንዳ በዓል ተሳታፊዎች አሸንዮዬን የሚሰሩት ምናቸው ላይ ነው?

South West Academy

A. አንገታቸው ላይ C. ዳሌያቸው ላይ
B. ደረታቸው D. እግራቸው ላይ

334. እንሶስላ_____ ክፍት ቦታው በትክክል የሚያሟላው የትኛው ነው?
A. ይቀባል B. ይበላል C. ይለበሳል D. ይሞቃል

335. የአሸንዳ በዓል ስርዓታዊ የአከባበር ቅደም ተከተል የያዘው የትኛው ነው?
A. ለፈጣሪ ምስጋና ማቅረብ፣ በየቤቱ እየዞሩ መጨፈር፣ ባለትዳር ወደሆነች ጋደኛቸው ቤት መሄድ፣ በዓሉን በድምቀት መሸኘት።
B. ለፈጣሪ ምስጋና ማቅረብ፣ ባለትዳር ወደሆነች ጋደኛቸው ቤት መሄድ፣ በየቤቱ እየዞሩ መጨፈር፣ በዓሉንበድምቀት መሸኘት
C. በየቤቱ እየዞሩ መጨፈር፣ ባለትዳር የሆነችው ጋደኛቸው ቤት መሄድ በዓሉን በድምቀት መሸኘት፣ ለፈጣሪ ምስጋና ማቅረብ
D. ባለትዳር ወደ ሆነችው ጋደኛቸው ቤት መሄድ፣ ለፈጣሪ ምስጋና ማቅረብ፣ በየቤቱ እየዞሩ መጨፈር፣ በዓሉን በድምቀት ማሸኘት

336. በአሸንዳ በዓል የወንዶች ሚና ምንድነው?
A. የትዳር ጋደኛ መምረጥ C. ሴቶችን ከጥቃት መጠበቅ
B. ቡድን ለይተው መጨፈር D. ልጃገረዶችን በዜማ ማወደስ

337. የአሸንዳ በዓል ለስንት ቀን (ቀናት) ይከበራል
A. ለሁለት ቀናት ለአንድ ቀን C. ለአንድ ቀን
B. ለአራት ቀናት ለሶስት ቀናት D. ለሶስት ቀናት

338. የአሸንዳ በዓል ለአሸንዳ ሴቶች የነፃነት ቀናቸው ነው የተባለው ለምንድ ነው?
A. የት ዋላችሁ ተብለው ስለማይጠየቁ C. በየቤቱ እየጨፈሩ ስጦታ ስለሚያገኙ
B. አባቶቻቸውንና እናቶቻቸውን ስለሚያከብሩ D. ቡድን መስርተው ሰለሚጨፍሩ

339. አሳዲ ለሚለው ቃል ፍቺ ሊሆን የሚችለው ከሚከተሉት መካከል የትኛው?
A. ኩል B. ሴራሚዜ C. ያገባች ሴት D. ኮረዳ

340. የምንባቡ ይዘት ከሚከተሉት መካከል የትኛውን ያንፀባርቃል?
A. ኢኮኖሚን B. ባህልን C. ማህበራዊ ኦሮን D.ሃይማኖትን

ምንባብ

የአሸንዳ ጭፈራ

የአሸንዳ ጭፈራ ከነሀሴ 16 እስከ 19 እስከ 19 ባሉ ሶስት ተከታታይ ቀናት ይከበራል። በዓሉ በዋነኝነት የልጃገረዶች በዓል ነው። ትዳር የመስረተች በአሸንደ ጭፈራ አትሳተፍም። በዓሉ የመስከ በዓል በመሆኑ የአሸንዳ ሴቶች የት ዋላችሁ ተብለው የማይጠየቁበት የነፃነት ቀናቸው ነው። በአሸንዳ ፍቅራቸውን የሚገልፀብት፣ መንደሮቻቸውን የሚያደምቁበት፣ አባቶቻችውን እና እናቶቻቸውን የሚያከብሩበት ህዝባዊ በዓል ነው።

ለበዓሉ ውስን ቀናቶች ሲቀሩ ሴቶች ቡድን ይመሰርታሉ። ቡድኑ በአብሮ አደግ ልጃገረዶች የአንድ መንደረ ልጆች ይዋቀራል። እነዚህ አብሮ አደጎችም ሴረ-ሚዜዎቹ የሚወጡ ዘፈኖችን ይቀበላሉ። ቡድኑን ያነቃቃሉ። የቡድኑ አባላት በዓሉ ሊጀምር ቀናቶች ሲቀሩ ለበዓሉ ድምቀት የሚሰጡ የሴት መጋጌጫዎች እንደኩል፣ በዳሌያቸው የሚያስሩት አሸንድየ በመቁረጥና እንሶስላ ዝግጅቱ ይጀምራል። በበዓሉ ቀንም አሳዲዊቹ (ኮረዳዎቹ) ፀጉራቸውን ቅቤ ተቀብተው እንሶስላቸውን ሞቀው፣ በበኩላቸው ደምቀው፣ በአገር ባህል ልብሳቸው አሸብርቀው፣ በዳሌያቸው ዙሪያ አሸንድየ አስረው ከበሮዋቸውን እየመቱ በገላጣ ሜዳ ላይ ይሰበሰባሉ።

South West Academy

በበዓሉ መጀመሪያ ቀን በአቅራቢያቸው በሚገኝ ቤተ-ክርስቲያን በመሄድ ለፈጣሪያቸው ምስጋና ያቀርባሉ። በመቀጠልም አምና የቡድኑ አባል የነበረች ነገር ግን ዘንድሮ ባለትዳር የሆነችው ጓደኛቸው ቤት በመሄድ የአሸንዳ ጥፍራቸውን ያሳያሉ። ጓደኛቸውን ያወዳሷታል። ትዳሯ ያማረ፣ ዘሯ የተባረከ እንዲሆን በዜማና ግጥማቸው ይመኙላታል። ሙሽራዋም ሚዜዎቿ እንዲሚመጡ ስለምታውቅ ቀድማ የሚበላ ነገር ታዘጋጃለች። ያዘጋጀችውንም ምግብ እንዲመገቡ ታደርጋለች በመቀጠልም ስጦታ ትሰጣቸዋለች።
አንዳንዳ ቡድን ከሚዜያችው ቤት አሀዱ ብለው የጀመሩት የአሸንዳ ጭፈራ በመዞር ለሁበረተሰቡ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክታቸውን በጭፈራቸው ያስተላልፋል። በምላሹም መለስተኛ ስጦታዎች ያገኛሉ። በዓሉ ለሁለት ቀናት በድምቀት ይከበራል። በሁለት ቀናት ውስጥ ከሁበረተሰቡ የተለያዩ ስጦታዎችን ወንዝ ተሻግረው በየጎጡ ስለሚዞሩ ወንዶችም ያጅቧቸዋል። ይጠብቋቸዋል። በሶስተኛው ቀን ሁሉመ የመንደሩ የአሸንዳ ቡድኖች ላይ በመሰባሰብ ነፃ የጭፈራ ቀን ያከብራሉ። ጭፈራውም በወዝ ዳርባሉ አዳ (ዋርካ) ዛፍ ስር ይሆናል። በመጨረሻም ለከርሞ በሰላም እንዲያገናኛቸው ተመኝተው በዓሉን በድምቀት ይሸኙታል።

ምንጭ፡- ክብሮም አሰፋ ሞላ። 2005 ዓ.ም
የራያ ህዝብ ባህልና ታሪክ። አ.አፋርኢስት
ማተሚያ ቤት ፣ ከገፍ 137 -140 በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ

ከጥያቄ **1** እስከ **11** ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሰረቱ ናቸው።
ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

ምንባብ

የሰው ልጅ ምግብ አብስሎ ለመብላት እና ራሱን ከአደጋ ለመከላከል አሳት ከፊጠረበት ጊዜ አንስቶ የስራ ፈጠራ ባለቤት ነበር ብሎ መናገር ይቻላል። በጥንታዊው የሰው ልጅ የኢኗር ስርዓትውስጥም ከተፈጥሮ ጋር በነበረው ግንኙነት ራሱን ለማኖር ደመነፍሳዊ ከሆኑ እንቅስቃሴዎች ወጥቶ የድንጋይና የእንጨት መሳሪዎችን መጠቀም በጀመረበት ጊዜ የስራ ፈጠራ ነበር። በጊዜ ሂደትም ትናንሽ ከምንላቸወ የፊጠራ ስራዎች ጀምሮ ታላላቅ እና እጅግ አስደናቂ የሚባሉ በርካታ ፈጠራዎችን አከናውኗል።

የስራ ፈጠራ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን የማፍለቅ ወይም የመፍጠር ጥበብ ነው። በአገራችን የአክሱም ሀውልትን የላሊበላ ውቅር አብያት ክርስትያናትን፣ የሀረር በርንና ሌሎችን ማየት ለፈጠራ ስራ በቂ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል። ይህም ኑሮን በተሻለ ለመኖርና ጣፋጭ ለማድረግ ካለን የሰው ልጆች ተፈጥሮአዊ ከሆነ ባህሪ የሚመነጭ ነው። በሌላ በኩል አዲስ ነገርን መፍጠር አሁን አገልግሎት የሚሰጠንን የፊጠራ ስራ በተሻለ መንገድ አገልግሎት ሊሰጠን በሚችል ሁኔታ እንደገና አሻሽሎ መስራትም ነው። በሌላ አገላለፅ በኑሮ ሂደት የሚያጋጥሙ ውጣውረዶችንና ችግሮችን በማቃለል ኑሮን ቀላል ማድረግ ነው። ቀደም ሲል ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ ለመንቀሳቀስ በእግር ቢኬላም በፈረስና በበቅሎ የመጓጓዝ ሁኔታ ነበር። በዚህ ዘመን ደግሞ እጅግ ፈጣንና ምቹ የሆኑ የምድር፣ የባህርና በአየር የሚቀሳቀሱ በርካታ የትራንስፖርት መገልገያ መሳሪያዎች ተፈጥረዋል። ይህም ቀደም ሲል እናጠፋው የነበረውን ጊዜ፣ ገንዘብና ጉልበት በመቀነስ በፈለግነው ጊዜ የፈለግነው ቦታ ያለምንም ድካም በመድረስ የምንፈልገውን ተግባር እንድናከናውን አስችሎናል።

በአንድ አገር የስራ ፈጠራ መስፋፋት ወሳኝ ነገር ነው። የስራ ፈጠራ እንዲስፋፋ ደግሞ ምቹ ሁኔታዎች መኖር አለባቸው። እነዚህ ምቹ ሁኔታዎች ውስጣዊ ውጫዊም ሊሆኑ ይችላሉ። ከእነዚህ ምቹ ሁኔታዎች መካከል የዜጎች የስራ ፍቅርና ተነሳሽነት እንዲሁም ለዘርፉ መስፋፋት ጠቃሚ የሆነ የመንግስት ፖሊሲ መኖር ዋናዎቹ ናቸው። በአደጉና ባላደጉ አገሮች አሁን የሚታየው የዕድገት ልዩነት መሰረቱ የስራ ፈጠራ መስፋፋትና አለመስፋፋት ላይ የተመሰረተ ነው። ለዕድገት ዋና መሰረት የስራ ፈጠራ መሆኑን በአግባቡ የተረዱ ለስራ ፈጠራ ትልቅ ግምትና ትኩረት ይሰጣሉ። የስራ ፈጠራ እንዲያድግና እንዲስፋፋም የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋሉ።

በተለይ አሁን ባለንበት የቴክኖሎጂ ዘመን የገበያው ፍላጎት ተለዋዋጭና እጅግ ፈጣን እንቅስቃሴ በሚታይበት ኢኮኖሚ ውስጥ ያለስራ ፈጠራ በገበያው ውስጥ ብቁ ተወዳዳሪ መሆን አይቻልም። የደንበኞች ፍላጎት የቴክኖሎጂውን ምጥቀት እየቀደመ፣ ቴክኖሎጂውም የደንበኞችን ፍላጎት አስቀድሞ በመተንበይ አዳዲስ የስራ ፈጠራዎችን ወደ ገበያ እያቀረበ በገሰገሰ ቁጥር የስራ ፈጠራ አስተሳሰብን መላበስ የበለጠ ጠቀሜታ አለው።

ምንጭ፤ ተፈራ ሙሉነህ። *2007*። የስራ ፈጠራና የብልፅግና ጥበብ። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ የግል ማህበር ከገጽ *2-6* ካለው ተሻሽሎ የተወሰደ።

341. የምንባቡ የመጀመሪያ አንቀጽ ትኩረት የሚያደርገው ስለምንድነው?
A. ስለሰው ልጅ ታሪክ B. ስለአደጋ መከላከል C. ስለስራ ፈጠራ D. ስለጥንታዊ ሰው

342. በምንባቡ የመጀመሪያ አንቀፅ ውስጥ በዕውቀትና በጥበብ አለመመራትን የሚያመለክተው ቃል የትኛው ነው?
A. ጥንታዊ B. ደመነፍሳዊ C. ተፈጥሮአዊ D. ስርአታዊ

343. በሁለተኛው አንቀጽ ውስጥ፣ የሰው ልጅ ከቦታ ወደ ቦታ መንቀሳቀስን ቀላል ለማድረግ የተጓዘበትን መንገድ የሚያሳየው ከሚከተሉት የትኛው ነው?
A. አንድ እግር፣ ሁለት እግር፣ አራት እግር፣ በአየር መጓዝ
B. በታክሲ፣ ከአውቶቡስ፣ በባቡር፣ በአየር፣ በእግር መጓዝ
C. በብስክሌት፣ በእግር፣ በበቅሎ፣ በአየር በምድር መጓዝ
D. በእግር፣ በበቅሎ፣ በመኪና፣ በመርከብ፣ በአየር መጓዝ

343. አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን ስራ ላይ የማዋል ጥበብ እንደሆነ ተደርጎ የተገለፀው ምንድነው?
A. የስራ ሂደት C. የፈጠራ ስራ
B. የትራንስፖርት መገልገያ D. የእክሱም ሀውልት

344. ለስራ ፈጠራ መስፋፋት እንደምቹ ሁኔታዎች የተጠቀሱት ምንድናቸው?
A. የዜጎች የስራ ፍቅርና የመንግስት ፖሊሲ C. የቴክኖሎጂና የደንበኞች ፍላጎት
B. የውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች መሟላት D.የዜጎችተነሳሽነትና የገበያ ፍላጎት

345. በሀገራት መካከል ለሚታየው የእድገት ልዩነት እንደምክንያት ተደርጎ የተወሰደው ምንድን ነው?
A. የቴክኖሎጂ ወደ ሀገር ውስጥ መግባትና አለመግባት
B. የትምህርት ስራ እንቅስቃሴ መዳበርና አለመዳበር
C. የስራ ፈጠራ መስፋፋትና አለመስፋፋት
D. የስራ ፍጥነትና ዝግመት

346 የቴክኖሎጂው ዕድገት የደንበኞችን ፍላጎት አርክቶ መገኘት እንዳለበት የሚገልፀው አንቀጽ የትኛው ነው?
A. አንደኛው B. ሁለተኛው C. ሶስተኛው D. አራተኛው

347. ለቀረበው ምንባብ ርዕስ ሊሆን የሚችለው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?
A. የቴክኖሎጂ መስፋፋት B. የስራ ፈጠራ C. የገበያ ፈላጎት D.የዕድገት ጎዳና

348. በምንባቡ ሃሳብ መሰረት የስራ ፈጠራ ለዕድገት መሰረት መሆኑን የተረዱ አገሮች ምን ያደርጋሉ?
A. ለስራ ፈጠራ ትኩረት ይሰጣሉ፣ ድጋፍም ያደርጋሉ።
B. ፋብሪካ ይገነባሉ፣ ምርት ይሰበስባሉ።
C. ገበያ ያስፋፋሉ፣ ድህነትን ይጠየፋሉ።
D. የስራ ተነሳሽነት ያሳያሉ፣ ኢኮኖሚን ይገነባሉ።

349. ምንባቡ ለሰው ልጅ የስራ ፈጠራ መጀመሪያ እንደሆነ አድርጎ ያቀረበው ምንድን ነው?
A. የድንጋጥ መሳሪያን መፍጠር C. እሳትን መፍጠር
B. የእንጨት መሳሪያን መፍጠር D. የአደን ቁሳቁሶችን መፍጠር

350. በሀገራችን ለፈጠራ ስራ በምሳሌነት ስለተጠቀሱት ነገሮች የሚነገረው ስንተኛው አንቀጽ ነው?
A.አንደኛው B. ሁለተኛው C. ሶስተኛው D. አራተኛው

South West Academy

South West Academy